# በነዚያ ዐይኖች ውስጥ ጅግኖችን አየሁኝ!

## ወንድ የወለዳችሁ ዋጡ መልሣችሁ፤ ለእኔ አላማረኝም የዐይን አገላለጡ።



ሙሾ ደርዳዋ ይህቺን ስንኝ የቋጠረችው የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ ም ዕልቂት ለመግለጽ ነበር።ወጣት ኢትዮጵያውያን አበረሀ ዶቦጭና ሞገስ አስግዶም በአዲስ አበባ ከተማ በግራዛኒ ላይ ቦንብ ወርውረው ያቆስሉታል።በዚያ ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ የወንድ ፆታው ያለው እየተፈለገ ይገደል ነበር። የጊዜውን አስከፊነት በአንድ ወቅት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በአንድ ስብሰባ ላይ በንግግራቸው መሐከል 'እኔም ወንድ ሆኜ እናቴ በአልጋ ሥር ሸሽጉኝ' ሲሉ ጠቅሰውታል።

እኔም በዐይነ ልቦናዬ ወደኋላ መለስ ብዬ ስመለከት፤ በፋሽሽት ጥይት ለመገደል ሲዘጋጁ ሞትን እንደ አንድ ሲኒ አቦል ቡና ቆጥረው፣ ' ቡና ስጠኝ' ያሉትን ራስ ደስታ ዳምጠውን አስተወሰኝ። ለፋሽሽት ጥይት ጉዳይ ያልሰጡትን አቡነ ጴጥሮስን እንዳስብ አደረገኝ። በፋሽሽት አደባባይ በሮማ ከተማ ሰንደቃ ዓለማውን፣ አረጓዴ፣ ቢጫው፡ ቀዩን፣ እርገጥ ሲባል አሻፈረኝ ብሎ፤ የፋሽሽቱን ጎራዴ ቀምቶ የፋሽሽት መንጋ ሲያጎራድደው ዘራይ ደረስ ታየኝ።
በሰሞኑ በጋዳፊ ቤተሰብ መላ ሰውነቷ ለፈላ ወሃ የተዳረገውን የሸዋዬ ሙላህን ዐይኖች ሰመለከት እላይ የጠቀስኳቸውን ጅግኖች ዐይኖች ነበር ያየሁት። እነዚያ ዐይኖች እንባን አላቀረሩም፣ ወይም አላወረዱም፣ የመንፈስን መሸበር ወይም የተሰፋ መቁረጥ ምልክት አላሳዩም። በግልባጩ ቆራጥነትን፣ አልበገር ባይነትን፣ በራስ መተማመንን ነበር የሚያሳዩት። በሸዋዬ ሙላህ ልብ ውስጥ የሚፈሰው ደም እነዚያ ቆራጦች በዱር በገደሉ አጥታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍሰው የዛሪቱን ኢትዮጵያ ያቆዩልንን መንፈስ ነበር የሚያጸባርቀው። ያ! በመሆኑ ነው በዓለም ዙሪያ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያለ ሁሉ ባርኔጣውን ለሸዋዬ ሙላህ ያነሣለት። በዓለም ዙሪያ ያለን ኢትዮጵያውያን 'ሐርከ ፉኔ' ኮራንብሽ አንላለን።

ስለ ወገኖቼ ኢትዮጵያውን ግን ብዙ የምለው ነገር ቢኖረኝም፣ ስለ ሸዋዬ ስቃይ ያልተሰማኝ ሰለሚየሰመስለኝ ትንሽ ልበል።

በወገኖች ላይ በውጪ ሃገር ሰው ግፍ ሲፈጸም ዳር እስከ ዳር በአንድነት ቆመን ተቃሞ እናሰማለን። ይህም ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው የሚያደርገው ነው። በተፈጥሮ ግማሽ እርግዝና የለም ። ግማሽ ሰቆቃም። እስቲ ወደኋላ መለስ ብለን የትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር መሪ መሰስ ዜናዊ ዳኛ ብርቱካን ሜዴክሳ ላይ ያደረሰባትን ለኢቲቪ ጋዜጠኛዋ ቃለ መጠየቅ መልስ ስትሰጥ በፊቷ ላይ የሚነበበውንና ሸዋዬ ሙህላ ለሲ ን ን ቃለ መጠየቅ መልስ ስትሰጥ በፊቷ ላይ ይነበብ የነበረውን አወዳድሩት፤ የቱን ያህል እርስ በእርስ እንደምን ጎዳዳና ለሃገራችን ውድቀት ለራሳችን ሰቆቃ ለኑራችን ሲፆልነት ምክንያቱ እኛው መሆናችንን ፍንትው አድርጎ ያሳያል።ከሁለቱ ሴቶች

በማን ላይ ነው ትልቁ ሕመም የሚታየው? እስር ቤቶቻችንን እንጎብኝ፤ በመንግሥት ግልበጣ ስም የታሰሩትን እማዋሸ ዓለሙን፣ ርዕዮት ዓለሙን፣ በኦጋዴን በወያኔ ወታደር ለሰባት ተደፍራ ጽንሷ ሰለአሰወረዳት ምን እንላለን? የጋዳፊ ቤተሰብ ሸዋዬ ሙላህን የወጭ ዜጋ ስለሆነችና ስለዜግነቷም ተቆርቋሪ ባለመኖሩ ያ ግፍ ተፈጸመባት።

ሰማኒያ ሚሊዮን ሕዝብ ባለበት ያወቁ የተማሩ በዓለም ዙሪያ በታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩ ሙሑራንን ያፈራች በታሪኳ ጥንታዊ የሆነች የኢትዮጵያ ዜጎቿ በሃገራቸው በአንድ ወንበዴ ቡድን ወያኔ በሚል በመለስ ዜናዊ የሚመራ ሲያዋርዳት ለምን ዝም ተባለ? በእርግጥ ጩህቴ ለራሴ ወይስ ለሸዋዬ? ይህንን እያንዳንዳችን ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ይሆናል። የራሳችንን ጉድፍ ሳናስወግድ ስንቀር ሌላው ሌላ ጉድፍ ቢያራግፍብን ምን ይደንቃናል?
የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ 1949 ዓ ም በዓለም በዲፕሎማሲው መድረክ ሊቢያ እንደሐገር እንደትቆጠር ይከራከሩ የነበሩት። ሊቢያ በኢጣሊያን ተቀጥቅጣ እየተገዛች ነበር። ኢትዮጵያ በዚያን ዘመን በምን ደረጃ ላይ እንደነበረች መገመት አያስቸግርም። ሊቢያ በቻ አይደለችም፤ መላውን የአፍሪካ አገሮች ቆመን ጠበቅናቸው ተተውን አለፉ። ይህ የማይቆጨው ዜጋ ያንን ለመመለስ ሐላፊነት የማይቀበል ለሸዋዬ ቢያለቅስ ማስመሰሉ ነው። ግን የሚያለቅሰው ለራሱ ነው።
ዛሬ የሸዋዬ ሙላህ በፈላ ወሃ መቃጠል በዓለም ዙሪያ ከደቂቅ እስከ ሊቅ መነጋገሪያ የሆነው የድመትና የውሻ መብት በተጠበቀበት ዓለም እንዴት በሰው ልጅ ላይ ይህን መሰል ግፍ ይፈጸማል በማለት ነው።

ለእኛ ለኢትዮጵያን ግን የሸዋዬን ጉዳይ የመጀመሪያውና ይህ ብቻ እንደሆነ ከማራገብ ይልቅ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሸዋዬዎች በሃገር ቤት ስላሉ ለዚያ ያበቀንን የወያኔ መንግሥት ለማስወገድ መስራት ይጠበቅብናል። የግፉ ምንጭ ያለው ሃገር ቤት ነው።የነ የፌዝ ዶክተሮች ወያኔዎች የሸዋዬ ሙላህን ደም መላሽ መስሎ ለመታየት ዘጭ እንበጭ እያሉ ነው። ‘ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባ’ እንዲሉ እድሉ ከተሰጣቸው የእርሷን ጉዳይ ለምን የገቢ ምንጭ አያደርጓትም? ቀድሞም የላኳት በሽያጭ መልክ ነበርና። እኛ ኢትዮጵያዊያን ‘የራሳችን ሰው ከሆነ ያሰቃየን፣ የወጭ ከሆነ ለምን?’ የሚለውን የሰነልቦና አመለካከት ድርቀት መዋጋት አለብን። ያለበለዚያ በሚለዮኖች የሚቆጠሩ ይሰደዳሉ በየቤቱ የሸዋዬን ዓይነት ሰቆቃን ይቀበላሉ። ለዚህ ሁለ ምንጩ በሃገር ውስጥ በዜጎች ላይ በትግራይ ጎጀሌዎች በሚፈጸመው የአስተዳደር በደል ነው። ይህ በደል ብዙ ዓመታት አስቆጥሯል፤ እንዴት ማስወገድ ይቻላል? የኢትዮጵያ ሕዝብ ከገባበት የስነልቦና አሸክላ ለመውጣት ከብቃትም በላይ ብቃት እንዳለው አንዷ ሸዋዬ ሙላህ ምስክር ናት።
ሸዋዬ አሜሪካዊ ወይም ኢግሊዛዊ ብትሆን ኖሮ የነዚህ ሃገራት የስነልቦና ሙሑራን የአእምሮዋን ኃይል የመንፈሷን ጥንካሬን እያደነቁ ለተማሪዎቻቸው ያስተምሩም በመጽሐፍ ያወጡት ነበር። በመስኩ የተሰማሩ የሃገራችን ሙሑራን ሳያጤኑት እንደማይቀሩ ተሰፋ አደርጋለሁ።
ሸዋዬን መሰል ጠካራ አእምሮ በዚያች ድንግል ሃገር አሁንም አለ። ወደ እርስ በርስ መጎዳዳት ምቀኝነት መከዳዳት ባናውለው ማለቴ ነው።

የመንግሥቱ ኃይለማሪያም ያንን አፍላ ወጣት እየገደለ በአውራ ጎዳኖች መጣሉ ስናስታውስ መለስ ዜናዊ ከመንግሥቱ በከፋ መንገድ የዜጎችን የአእምሮን የፈጠራ ችሎታ የሚያመክን፤ለዘለቂታው ትውልድን የራሱ ባለቤት እንደይሆን ለማኝ ተመጽዋች ሌባ ውሸታም ፋዞ ሆኖ እንዲቀር የሚያደርግ ነው። ሁለቱም መሪዎች የአእምሮ በሽተኛ ናቸው። ዜጎች በነፃነት እንዳያሰቡ አይፈልጉም።ዜጎች ለማሰብ እንኳን ቢሞክሩ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ በካንብ አጉረው የሚቀልቡትን ሠራዊት የሚያቀሳቀሱ ናቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ጉዳይ በራሱ የመወጣቱ ጉዳይ አሁን ነው። ሸዋዬ መላሕ አይነት ሰቆቃ በሃገርም ከሃገርም ውጪም በየደቂቃው የሚፈጽም ስለሆነ ይህን ማስቆም በያንዳንደችን ትከሻ ላይ ያረፈ ሐላፊነት ነው። ብንሸሸውም ችግሩ በየአለንበት በራችንን አኳክቶ እየመጣ ነው። ከኢትዮጵያ መጥታ በሃርቨርድና ኦክስፎርድ የምትማር ወጣት ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ለማለት ትችላለችን? ይህችን የመሰለች ኢትዮጵያ ያቆያትን አባቷን ግን ከመውቀስ ወደኋላ አትልም። በአርብ ቤቶች ተቀጥረው በግርድና ከእንሰሳ በታች የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ይህቺን መሰል ሃገር ያቆዩትን አባቶች መውቀሳቸው አይቀርም።

በሃገራችን በ1966 ዓ ም በገባው ረሐብ ምክንያት፤ሰዎች ' ረሃብን ሳናጠፋ ልጅ አንወልድም' ይሉ ነበር። ቆየት ብሎ ደግሞ በደርግ ዘመን ሰላም ሳይሰፍን ለጦርነት ልጅ አንወልድም' ብለው ነበር። በወያኔ ደግሞ ለግርድና ፣ ለጉዲፈቻ ፣ ለባርነት፣ ለሽያጭ ልጅ አንወልድም' እያሉ ነው። ወዴት እያመራን ነው? መልሱን ለእናንተ ልተወው።

ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca